# እነ ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ አላማቸው ምንድነው?



ባንዳው ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ

ከአስራ ስምንት ወራት በፊት የኢትዮጵያ አገራዊ ንቅናቄ የሚል ስብስብ ተፈጥሮ ነበር። በዚያ ስብስብ ውስጥ የእነ ሌንጮ ድርጅት (ODF) ኦሮሞን ወክሎ፣ ግንቦት 7 ብሔሩን ወክሎ፣ አንድ የሲዳማ ድርጅት እና አንድ የአፋር ድርጅት ተገኝተው ነበር። በተጨማሪም አንድ ወልደ ገብርኤል የተባለ ግለሰብ ከ50 ሚሊዮን በላይ የሚሆነውን አማራ ወክሎ ተሳትፏል። “አማራ በግለሰብ የተወከለው ጠንካራ ድርጅት ስለሌለው ነው” የሚል ምክኒያት መሰጠቱንም እናስታወሳለን። የኋላ ኋላ ነገሩ ያስጠቃቸው መሆኑ ሲገለጽላቸው ወደፊት የአማራ ድርጅት እንደሚቋቋም እንደሚያደርጉ ወይንም እንደሚያቋቁሙ አቅጣጫ ሰጥተው ነበር።

በወቅቱ በንቅናቄው ውስጥ ከተሳተፉት ድርጅቶች ያልተናነሰ አቅም የነበራቸውና ድምጻቸው እንኳን ተሰምቶ ከማይታወቀው ከሲዳማና ከአፋር ድርጅቶች ይልቅ በሕዝብ ዘንድ እውቅና የነበራቸውና ከብሔር ግንቦት 7 እና ከእነ ሌንጮው የኦሮሞ ድርጅት መሳ-ለ-መሳ መሰለፍ የሚችሉ ከሦስት በላይ የአማራ ድርጅቶች ነበሩ እነርሱም ቤተ-አማራ፣ ዳግማዊ መዐሕድ እና አኅመን ናቸው።
አገራዊ ንቅናቄው ያስፈለገበት ምክኒያት ወያኔ በሕዝባዊ አመፅ ለመውደቅ ጫፍ ደርሶ ስለነበርና በተለይ የአማራ ተጋድሎ አይሎ ህወሓት መራሹን አምባገነን ፋሽስት ተናንቆ ሊያስወግደው የነበረ ሥለሆነ የምኒልክን ቤተ-መንግስት አማራ እንዳይገባበት በአቋራጭ ለመያዝ ነው። የዲያስፖራ “አንድነት” ፖለቲካ አስቂኝ ጎኑ ይህ ነው እዛው “ኢትዮጵያ” በምትባለው ምድር ውስጥ ያለው ከሃምሳ ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ከሕልውና አደጋ ሳይላቀቅ እነርሱ የምኒልክን ቤተ-መንግስት አማራ ይይዘዋል በሚል መከራቸውን ያያሉ።

የንቅናቄው አድራጊ ፈጣሪዎች ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስና ፕሮፌሰር ጌታቸው በጋሻው ከዚያን ጊዜ አንስቶ ያለዕረፍት ለአማራ ድርጅት ሊፈጥሩለት በመድከም ላይ ናቸው። በአንድ ወቅት ቤተ-አማራን፣ ልሣነ-ግፉዓን የወልቃይት ማህበርን፣ ሞረሽን እና አንዳንድ በአማራ ስም የሚንቀሳቀሱ አክቲቪስቶችንና ጋዜጠኞችን ጨምረው ውይይት አድርገው እንዲቀላቀሉ ጥረት ተደርጎ ነበር፤ ንሥሮቹ የቤተ-አማራ ልጆች ነገሩን ሲቃወሙ ቀረ እንጅ የሥራ ድልድል ሁሉ ተደርጎ በሕዝብ ግንኙነት እና መሰል ቦታዎች ሰዎችን መጠቆም ሁሉ ተጀምሮ ነበር፤ ነገሩ አላምር ሲል የሞረሽ ተወካዮችም እንደ ቤተ-አማራ ተወካዮች አይ ይሄ ነገር ብለው አፈነገጡ ልሣነ-ግፉዓንም ሁለተኛ እንዳትጠሩን ብለው ፍርስርሱ ወጣ ሴራው ከሸፈ!

ይህ ዘዴ እንዳልተሳካ ያወቁት እነ ሻለቃ ዳዊት ዳግማዊ መዐሕድን በኢሳት የአየር ጊዜ ሰተው እነማናችሁ ምንድናችሁ አሏቸው። አመላለሳቸው ስላልጣማቸው የቃለ-መጠይቁን ሁለተኛ ክፍል አፍነው በስንት ግድ ለቀቁት! ከዛ በኋላ አይናቸውን በጨው ታጥበው ድርጅት ማቋቋሙን ተያያዙት! የነቃ የበቃው የአማራ ልጅ ሊጠጋቸው አልቻለም፥ ነገሩ በሩቁ ሸቶት "ወግድልኝ ትጣላኛለህ" ብሎ ተፀየፋቸው። አንዳንድ መልከስከስ የጀመሩ ግን ነበሩ ውግዘት ሲደርስባቸው ተመልሰው ሰከኑ እንጅ! ከሶስት ወር በፊት አካባቢ ደግሞ ዳግማዊ መዐሕድና ቤተ-አማራ መድኅን ተዋህደው የፈጠሩትን መዐሕድን ለመጠምዘዝ ሙከራ አደረጉ! ደብዳቤ ጽፈው ጠየቋቸው ከዛም አልፈው ሰነድ ልከው ይህንን ተቀበሉ ሲሉ የድፍረት ጥጋቸውን አሳዩ! መዐሕድ 'በአፍንጫሁ ይውጣ በአማራ አልደራደርም' ሲል እንደተለመደው በኢሳት አቅርበው ለማስወገዝ ጥረት አደረጉ እሱም አልተሳካም።

ከዛ በኋላ የወሰዱት እርምጃ አማራው ሊወደውና ሊደግፈው የሚሻውን ስም እና እንቅስቃሴ አጥንቶ መምጣት እንደሆነ በማመን የሚችሉትን ለማድረግ ሞከሩ። የመጀመሪያው የአማራ ድርጅቶች መሰረታቸው ውጭ መሆኑን በሶሻል ሚዲያውም ሆነ በተለያዩ አጋጣሚዎች አማሮች ያወራሉ በመሆኑም አገር ውስጥ ተመሰረተ ብንል እንታመናለን ብለው በማሰብ ከዚህ በፊት ወጣት አማሮች እውቅና አግኝተውበት የነበረውን ድርጅት ስም <<አ.ወ.ጋ.ን>>ን ለወጥ በማድረግ <<አ.ወ.ን >> ብለው መጡ! አልተሳካም! ንሥር አማራ እነማን እንደሆኑ ወዲያው ደረሰበት ተፀየፈው! እነርሱም ተመልሰው ወደ ጉድጓዳቸው ገቡ።

የሰሞኑ ደግሞ የጉድ ነው! ንሥሮቹ የአማራ ልጆች
"አንድ አማራ ለሁሉም አማራ፥
ሁሉም አማራ ለአንድ አማራ"
የምትል መርህና የትግል ቁልፍ አለቻቸው። ኅጠኝነትን እንከትክቷን ያወጧትና አርቀው የቀበሯት በዚህች መርሃቸው ነው። የእነ ሻለቃ ዳዊት አይንም ተወርውሮ ያረፈው ከዚህች መርህ ቃል ላይ ነው፤ "አንድ አማራ" ብለው መጡ። በእርግጥ ቅኔው ሲፈታ አንድ የአማራ ግለሰብ ማለታቸው ነው ምናልናትን ወልደ ገብርኤልን መልሰው ብቻውን ሳያመጡት አይቀርም።

የተለያዩ ድህረ ገፆችን ጨምሮ ህብር ራዲዮና ዋዜማ ራዲዮ ያቀረቡት ዜና "የአማራ የፖለቲካ ሃይሎች ግንባር ፈጠሩ" ይላል። ከዚህ ዜና ጋር ምስሉ የታተመው ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ ነው። የህብር ራዲዮ ዜና "ከዚህ ቀደም በተበታተነ መልኩ የሚካሄደውን ትግል በማቀናጀት በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ለመቀየርም ያለመ 'አንድ አማራ' በሚል በአዲስ አደረጃጀት መጥተዋል" ሲል አዲስ ድርጅት የተቋቋመበትን ምክኒያት ያስቀምጣል።

በግልፅ እንዳስቀመጡት ዓላማቸው ሥልጣን ላይ ያለውን መንግስት #መቀየር ነው። የአማራ ሕዝብ የሚፈልገው ግን ሥልጣን ቀያሪዎችን ሳይሆን ወያኔንና ፀረ-አማራ ቡድኖችን በሙሉ አስወግዶ የአማራውን ሕዝብ ሕልውና አስጠብቆ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙን የሚያስከበርለት ለዚህም እውን መሆን መስዋዕት የሚሆንለትና በስተመጨረሻም ሥልጣን ይገባኛል ብሎ ሌላ የስቃይ በትር የሚያደርስበት ሳይሆን ሥልጣን የአማራ ሕዝብ በመሆኑ የአማራ ሕዝብ በፈቀደው መልኩ እንዲኖር ወሳኝ አካልነቱን የሚቀበል ታጋይን ነው። የአማራ ሕዝብ በወጣት ልጆቹ በኩል ሥለአማራ ማንነቱ የሚታገልና ሕልውናውንም የሚያስከብር መሆኑን በየቀኑ

ግንባራቸውን ለጦር ደረታቸውን ለጥይት የሚሰጡ ልጆቹ እንደ ጎርፍ የሚወርደው ደማቸው ምስክር ነው። እነ ሻለቃ ወልደ ጊዮርጊስ በዚህ ደም የሚቀልዱት ምን ፈልገው ነው ብለን የምንጠይቀውም ለዚህ ነው!
Satenaw.com ህብር ራዲዮን ጠቅሶ ባስነበው ዜናው ላይ "የአማራ ዘውጌ ፖለቲከኞችን ወደ አንድ መድረክ እንዲመጡ ለማድረግ ላለፈው አንድ አመት ገደማ ድርድር እና ዝግጅት ሲደረግ እንደነበር መስራቾቹ ይናገራሉ" ይላል። ከላይ እንዳስቀመጥኩት ከአንድ አመት ከስድስት ወር ጀምሮ በአገራዊ ንቅናቄው ውስጥ እውነተኞቹን የአማራ ድርጅቶች ለመጠምዘዝ ጥረት አድርገው እንዳልተሳካላቸው አይተናል። በመሆኑም የተደረጉት ሙከራዎች ባለመሳካታቸው እራሳቸው ጠፍጥፈው ድርጅት ሰይመው መጥተዋል ማለት ነው "አንድ አማራ" ወይንም ዳግማዊ ብአዴን!
አዲሱ የድርጅት ሎጎም ሆነ ዜናውን በተልዕኮ የተቀባበሉት የሚዲያ አውታሮች "አንድ አማራ" ከየትኞቹ የአማራ የፖለቲካ ሃይሎች፣ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች እንደተመሰረተ አላወቅንም ብለዋል።

በአጠቃላይ በአንድ የራዲዮ ፕሮግራም ላይ ፀረ-አማሮች "በምንወደው ነገር ተመስለው ይመጡብናል" ሲል ትንታግ የአማራ ልጅ መሳፍንት ባዘዘው እንዳስቀመጠው እነሆ ዛሬ በምወደው ስም "አንድ አማራ" ብለው ተኩላዎች ተነስተዋል። አማሮች በተመስየዎች ልንሳሳት የማንችል ባለ ንሥር እይታ በመሆናችን ሁሉንም እየመረመርን የ"አንድ አማራ"ን ቀጣይ እርምጃ በንቃት እየተለታተልን እንገኛለን። እርግጥ ነው በእነ ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ የሚቋቋሙ ተመስየ ድርጅቶች እንደ ዝንብ ከሰባት ቀን የዘለለ ሕይወት እንደማይኖራቸው ይታወቃል።

**ቸር እንሰንብት!**
**ድል ለአማራ ሕዝብ!**
**ባየ ተሻገር (ነአኩቶለአብ)**